# የወያኔ የግንቦት 20 የቀዘቀዘ የበዓል አከባበርና ስውር ሽፍጡ!

ወያኔ ሥልጣን ከጨበጠ ጊዜ ጀምሮ የግንቦት ሃያ በዓል አከባበር እንደ ዘንድሮው (2010 ዓ.ም.) ፈዞና ደብዝዞ የሚያውቅበት ዘመን የለም፡፡ በርካቶች ይሄንን ሁኔታ ከወያኔ መሸነፍ ጋር አያይዘውታል፡፡ እውነቱ ግን ይሄ አይደለም፡፡ አዎ እርግጥ ነው ወያኔም እንዲህ ተደርጎ እንዲታሰብ ፈልጓል፡፡ ሌላው ሁሉ ቢቀር ግን ወያኔ የግንቦት 20 ን በዓል እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ መቀሌ ላይ ዷል አድርጎ በደመቀ ሁኔታ ማክበር ይችል ነበረ፡፡ ነገር ግን አላደረገውም፡፡ ያላደረገበት ምክንያትም ሰዉ ወይም ሕዝቡ ወያኔ ስለተሸነፈ እንደሆነ አድርጎ እንዲረዳው ስለፈለገ ነው፡፡ ግን ለምን??? ወደኋላ እንመለስበታለን!

ወያኔ በዓሉን በለመደው መልኩ ባለማክበር ብቻ አይደለም ስለተሸነፈ እንደሆነ እንዲታሰብ ለማድረግ ጥረት ያደረገው፡፡ ነገር ግን በዓሉን አስመለክቶ መቀሌ ላይ በአቶ ሥዩም መስፍን፣ በአቶ ጌታቸው ረዳና በአቶ ሕላዌ ዮሴፍ በተመራው ስብሰባ ላይ እነኝህ የወያኔ ባለሥልጣናት እያለቃቀሱ በተናገሯቸው ነገሮች ወያኔ ስለተሸነፈ እንደሆነ ለማስመሰል ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡

የወያኔ ባለሥልጣናት የማስመሰል ጥረታቸውም ሠምሮላቸው እንደ ኢሳት ያሉ የመገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኞችና ተንታኞች "የመቀሌው ስብሰባ እስከዛሬ የወያኔን መሸነፍ እንጠራጠር ለነበርን ወገኖች የወያኔ መሸነፍ እርግጥ መሆኑን ያረጋገጥንበት ጉባኤ ነው!" እስከማለት ደርሰው መታለላቸውን መሸወዳቸውን የሚመሠክሩ ንግግሮችን ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

የመቀሌው ስብሰባ የተደረገው በአማርኛ ነበር፡፡ ይሄ ያልተለመደ ነው፡፡ ጉባኤውን የመሩት ሦስቱም የወያኔ ባለሥልጣናት ትግርኛ ተናጋሪ በሆኑበት ሁኔታ እና የስብሰባውም ታዳሚ የትግራይ ነዋሪ እንዲሁም የሕወሓት ታጋዮች በሆኑበት ሁኔታ ስብሰባን በአማርኛ ማድረግ አዲስና ያልተለመደ ነው፡፡

ጉባኤው ክልል ከሚሏቸው የሀገሪቱ ክፍሎች የተጋበዙ እንግዶችን ሲያካትት ብቻ ነው መቀሌ ላይ የሚደረጉ ጉባኤዎች በአማርኛ የሚያኪያሒዱት፡፡ እሱም ቢሆን ሁሌም አይደለም አንዳንዴ ከሌላ ቦታ የመጡት ትግርኛውን አለመስማታቸው ሳያሳስባቸው በሚገርም ሁኔታ ጉባኤውን በትግርኛ ያደረጉበት ጊዜ ኖሮ ያውቃል፡፡

የቀደመው ልምድ እንዲህ በሆነበት ሁኔታ ነው እንግዲህ ወያኔ መቀሌ ላይ ያደረገውን የዘንድሮውን የግንቦት 20 በዓልን ያከበረበትን ስብሰባ በአማርኛ ያደረገው፡፡ ይሄም ሆን ተብሎ ነው፡፡ እንደ ኢሳት ያሉ የመገናኛ ብዙኃን በጉባኤው የተነገሩ ነገሮችን "እነኝህ የማስመሰል አባባሎች ዓላማቸው ምንድን ነው? ገልብጠን እንፈትሽ!" ሳይሉ፣ ወያኔ እያስተጋባው ያለው ነገር በተጨባጭ ካለው እውነታ ጋር ይጣጣማል ወይ? ብለው ሳይፈትሹ ሳይመረምሩ ወያኔ የሚወረውርላቸውን ፕሮፖጋንዳ (ልፈፋ) እንደወረደ ወያኔ በሚፈልገው መልኩ ተረድተው ያንኑ እንደሚያስተጋቡት ስለሚያውቅ ያንኑ እንዲያስተጋቡ ለማድረግ ታስቦ ነው ስብሰባው በአማርኛ የተደረገውና የማስመሰል ንግግሮችን ያደረጉበት ምክንያት፡፡

በስብሰባው ላይ በተለይ ኤርትራዊው የብአዴን አባል አቶ ሕላዌ ዮሴፍ የወያኔ ባለሥልጣናት በጡረታ እንዲገለሉ መደረጋቸውን በመቃወምና ቅሬታ በማሰማት ከተናገረ በኋላ፡-

* በጡረታ ብንገለልም ታጋይን ከሥራ ከበታ ዞር ማድረግ ይቻል ይሆናል ከትግል ዞር ማድረግ ግን አይቻልም! ከፖለቲካው ማንም ሊያገለን አይችልም! ታጋይንና ትግልን የሚለያቸው ሞት ብቻ ነው!

* የኢሕአዴግ አስተሳሰብ በመሸነፉ የአስተሳሰብ ግባችን fail አድርጓል፡፡

* ከ 27 ዓመት በፊት የተሸነፉ አስተሳሰቦች መልሰው አቆጥቁጠዋል፡፡

* የመሬት ፖሊሲ እንዲሁም የብሔር ሙብት የመጣስ አዝማሚያ እየታየ ነው፡፡

* የሚፈለገውና የምንፈልገው ነገር ለትውልድ አልተላለፈም፡፡ አዲሱ አመራር ይሄን አያውቅም፡፡

* ትምክህተኛና ጠባብ የሚሉ ቃላትን መጠቀም ነውር የሆነበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ገብተናል፡፡

* ኢሕአዴግ የመከፋፈልና የመሰነጣጠቅ አደጋ አጋጥሞታል፡፡

ሲል አቶ ጌታቸው ረዳ ደግሞ፡-

* የቀድሞው ሥርዓት አስተሳሰብ አሁን በተለይ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ብሔራዊ ጣቢያ ላይ እየተንጸባረቀ ነው ብሏል፡፡

አቶ ሥዩም መስፍንም በፖለቲካና በሕሊና እስረኞች መፈታትና በሒደቱ ቅሬታውን ከገለጸ በኋላ፡-

* ከገንዘብ ሙስና በላይ ዋናው ችግር የአመለካከት ሙስና ነው በማለት የዐቢይን አሥተዳደር በአመለካከት ሙስና ከሷል፡፡

እንግዲህ ይሄንን ይሄንን ሰዎቹ በስብሰባው ላይ የተናገሩትን የብዙኃን መገናኛዎቻቸውም ወደሕዝቡ እንዲህ በማድረስ ነበረ ሕዝቡ መስማት የሚፈልገውን ነገር እንዲሰማ በማድረግ ሕዝብን ለማቄል የተሞከረው፡፡

ለመሆኑ ግን ለምን ነበረ ወያኔ እንዲህ ዓይነት ንግግሮቹ ሕዝብ ዘንድ እንዲደርሱ በማድረግ ወያኔ የተሸነፈ መስሎ እንዲታሰብ የፈለገው? ተብሎ መጠየቅ ያለበት ይመስለኛል፡፡ መልሱ ደግሞ ወያኔ ያደራጀው የሐሰተኛው የዐቢይ የለውጥ አሥተዳደር ሐሰተኝነትና አሻንጉሊትነት እንዳይጠረጠር፣ እንዳይጋለጥ፣ እንዳይነቃበት ለማድረግ፤ ኃይል፣ ጉልበት፣ አቅም፣ ሥልጣን ያለው በማስመሰል ሕዝብ ከጎኑ እንዲቆም ለማድረግ ነው ሌላ ዓላማና ምክንያት የለውም፡፡

ይሁንና ግን ለመሆኑ የዐቢይ የለውጥ አሥተዳደር ለማታለል ለመሸወድ ካደረገው አደረኩት ከሚለው የእስረኛ ፍች በስተቀር ኃይለኛ፣ ባለጉልበት ባለሥልጣን ሆኖ የሕዝብን ጥያቄ ለመመለስ በሚያስችል ደረጃ ምን ለውጥ ሲያመጣ፣ ምን እርምጃ ሲወስድ፣ ምን የመመሪያ (የፖሊሲ) ውሳኔ ሲያስተላልፍና ሲያስፈጽም ዓያቹህና ነው ሐሰተኛውን የወያኔን የለውጥ አሥተዳደር ለውጥ እንዳመጣ ወይም እንደሚያመጣ የምታስቡት??? ሌላው ቀርቶ በጥገናዊ ለውጥ ደረጃ እንኳ የሚጠቀስ የለውጥ እርምጃ ሲወስድ ዓይታቹሀል ወይ??? ከሽንገላና ከባዶ ወሬ ውጭ ምን ያያቹሀት ነገር አለ???

ቆይ ግን ጋዜጠኛ ነኝ፣ ተንታኝ ነኝ፣ ፖለቲከኛ (እምነተ አሥተዳደራዊ) ነኝ፣ ምንትስ ነኝ፣ ቅብርጥስ ነኝ የምትሉና በዚህ የወያኔ ድራማ የተሸወዳቹህ ሁሉ፡-

ሲመስላቹህ የወያኔ ባለሥልጣናት እንዲህ እያለቃቀሱ መሸነፋቸውን በብዙኃን መገናኛ ሲያረዱ የትግሬ ሕዝብ ቅስም ይሠበርብናል፣ በቁጣ ይነሣብናል፣ ጭንቀት ውስጥ ይገባብናል፣ የራስ መተማመኑን ያጣብናል፣ ወኔ ይከዳዋል፣ ሥነ

ልቡናው ይላሽቅብናል፣ ለእኛ ያለውን ድጋፍ ይነሳናል.... ብለው የማይጨነቁ፣ የማያስቡ፣ የማይጠነቀቁ ይመስላቹሃል ወይ ምድረ ደነዝ ሆይ???

ደነዞቹ ሆይ! የወያኔ ባለሥልጣናትን በባሕርያቸው ስታውቋቸው የፈለገውን ያህል ሽንፈትና ውርደት ቢያጋጥማቸው እንኳ በዚህ መልኩ መሸነፋቸውን እየተናገሩ በከፍተኛ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ተውጠው የሚያለቃቅሱ ዓይነት ሰዎች ናቸው ወይ???

የወያኔን ባለሥልጣናት የትግሬ ሕዝብን በተመለከተ ከላይ የገለጽኩት ችግር ያላሳሰባቸውና ያላስጨነቃቸው የትግሬ ሕዝብ ወያኔ ምን አስቦ፣ ምን አቅዶ ምን እየሠራ እንደሆነ ውስጥ ለውስጥ እንዲያውቅ እንዲረዳና እንዲረጋጋ ስለተደረገና ይህ የወያኔ ስውር ደባ ውጤት እንደሚያመጣም ሙሉ በሙሉ ስለተማመነ ነው በወያኔ ባለሥልጣናት ለቅሶ ያልደነገጠው ያልደነበረውና የማይደነግጠውም እሽ እነ አህዮ???

እባካቹህ በተለይ የኢሳት ጋዜጠኞችና ተንታኞች ሆይ! የመረዳት አቅሙ ከሌላቹህ በቃ ዝም በሉ!!! እናንተ ተጃጅላቹህ፣ እናንተ ተሸውዳቹህ፣ እናንተ ተሳስታቹህ ሕዝብን አታሳስቱብን፣ አታጃጅሉብን፣ አታስሸውዱብን??? በዚህ ሰዓት የናንተን ያህል የወያኔ መጠቀሚያ የሆነ የለም!!! ምንጊዜም ቢሆን ከወያኔ በኩል የሚወጡ መረጃዎችን ፊት ለፊት በሚታየው ገጽታቸው አትረዱት፡፡ እውነቱ ከጀርባው ያለው ገጽታው ነው፡፡ እሱን ማየት ካልቻላቹህ እባካቹህ ዝም በሉ!!!

ሰው እንዴት በየቀኑ ይሸወዳል??? እስኪ ከዚህ ቀደም ከወያኔ "አፈትልኮ የወጣ!" እያላቹህ ያስተላለፋቹህትም ይሁን እንዲህ እንደአሁኑ ወያኔ በይፋ ከተናገረውና እንዳለ ተቀብላቹህ ካስተጋባቹህት ከጊዜ በኋላ ግን ሐሰት ሆኖ ከተገኘው ለመማር ሞክሩ??? ሰው እንዴት ከስሕተቱ አይማርም??? ነው ወይስ ወያኔ ገዝቶ ወስዷቹሃል???

እናም ወገን ሆይ! የለውጥ የወያኔ  አሥተዳደር የተባለውን የዐቢይን አሥተዳደር ፈጽሞ አትመን ውሸት ነው!!! ወያኔ ዘወትር እያለቃቀሰ እያስተጋባልህ ያለው ነገር ሁሉ መስማት የምትፈልገውን ነገር ነው እንጅ እየሆነ ያለውን ወይም የሚሆነውን አይደለም፡፡ እንዲህ እያደረገ ነው እያታለለህ ያለው፡፡ ይሄንን ልብ ማለት ይኖርብሃል!!! ለውጥ የተባለው ወይም የዐቢይ አሥተዳደር ሐሰተኝነትን ከእስከአሁኑ ቆይታው ካልተረዳኸው ያለጥርጥር ነገ የምታረጋግጠው ይሆናል፡፡ ነገ ስታረጋግጥ ግን ምንም ማድረግ የምትችልበት ዕድል አይኖርህምና እባክህን ተጨባጭ ለውጥ ሳታይ በባዶ ወሬና ሽንገላ የማይሆን ተስፋ ጨብጠህ ለውሸቱ የለውጥ አሥተዳደር እየሰጠኸው ካለው ድጋፍ ታቀብና ትግልህን አጠናክረህ ቀጥል!!!

አሁኑኑ ንቃና እምቢ በል!!! ኢሳትና ግ7 የዐቢይ/ወያኔ የለውጥ አሥተዳደር ሐሰተኛ መሆኑን በቀላሉ ማረጋገጥ እየቻሉ በጀርባ ሔደው ከዐቢይ/ወያኔ ጎን መቆማቸው ፍንትው ብሎ እየታየ ነውና ፈጽሞ እነሱን አትመን!!! ለሥልጣን ካልሆነ በስተቀር "ለሕዝብ ነጻነት ነው የምታገል!" የሚል ማንኛውም ኃይል በምንም ዓይነት ተአምር ቢሆን ከወያኔ ጋር በጎን ተደራድሮ ሊስማማ አይችልም!!! የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ተጠንቀቅ!!! በየዕለቱ እየካደህ ከወያኔ ጋር የሚሠለፈው ቡድንና ግለሰብ በርክቷል!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com